# ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ

**Coalition for Unity and Democracy Party (Kinijit)**

## «ትብብር ለነጻነት እና ለዴሞክራሲ»ን አስመልክቶ ከቅንጅት አለም አቀፍ የፖለቲካ አመራር ኮሚቴ የተሰጠ ማብራሪያ

የዚህ ማብራሪያ ዋና አላማ የቅንጅት አባላት፣ ደጋፊዎችና እንዲሁም አጠቃላይ ህብረተሰቡ::

- ትብብሩን በሚመለከት ማወቅ የሚገባቸውን ጭብጮች ለማቅረብ፣
- የቅንጅት አለም አቀፍ የፖለቲካ አመራር የትብብሩ አካል ለመሆን የወሰነበትን ምክንያት ለመግለጽ፣
- በትብብሩ ላይ ከተለያዩ አካላት የሚቀርቡትን መሰረታዊ ጥያቄዎች በማንሳት ምላሻቸውን ለመስጠት ነው::

### ሀ-- ትብብሩን የፈጠሩ ድርጅቶች

እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ከግንቦት 19-21 ሆላንድ ውስጥ በዩትሬክት ከተማ አምስት የፖለቲካ ድርጅቶች ተሰባስበው ትብብር ለሰላም እና ለዴሞክረሲ የተባለውን የጋራ ትግል ማድረጊያ አካል ፈጥረዋል:: እነዚህ ድርጅቶች

1- ቅንጅት ለአንድነት እና ለዴሞክራሲ ፓርቲ (ቅንጅት)
2- የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ )
3- የኦጋዴን ብሄራዊ ነጻነት ግንባር (ኦብነግ)
4- የሲዳማ ነጻነት ግንባር (ሲነግ )
5- የኢትዮጵያ ህዝቦች አርበኞች ግንባር (ኢህአግ) ናቸው::

በዚሁ አጋጣሚ የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኀይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ትብብሩን ለመፍጠር በተደረገው ውይይት ላይ በመገኘት በቀና መንፈስ ተካፍሎ ነበር:: ሆኖም ግን የትብብሩ አካል ለመሆን በአባል ድርጅቶቹ መሃል ሰፊ መመካከር የሚያሰልግ መሆኑን በማመላከትና ለውሳኔ እንዲረዳው የአንድ ወር ግዜ እንዲሰጠው በጽሁፍ ጠይቆ ከስምምነቱ የፊርማ ስርአት በፊት ተሰናብቷል:: ህብረቱ ግንቦት 14 1998 ባወጣው መግለጫም የትብብሩ አካል እንደማይሆን መወሰኑን አስታውቋል:: በቅንጅት በኩል በዚህ ውሳኔ ያዘንን ብንሆንም ትብብሩ ኅብረቱን እና ሌሎችንም በርካታ የፖለቲካ ድርጅቶች በማቀፍ ሁሉንም ያካተተ እንዲሆን ጥረታችን ይቀጥላል::

### ለ- የመተባበር ሃሳብ አጀማመር ታሪክ

የትብብር አስፈላጊነትን በሚመለከት በበርካታ ድርጅቶች እና በተለይ በኦነግ መሃከል ሲደረግ የነበረው ግንኙነት ረጅም ታሪክ አለው:: በቅንጅቱ ውስጥ ከተጠቃለሉት ድርጅቶች መሃል የቀድሞዎቹ መኢአድና ኢዴፓ- መድህን፣ ከዚህ ውጭም ህብረቱ እና በህብረቱ ውስጥ የሚገኙ ድርጅቶች የተለያዩ ሙከራዎች ሲያደርጉ ቆይተዋል:: ድርጅቶቹ ለምን እንዲህ አይነቱን ትብብር ለመፍጠር ሲፈልጉ እንደኖሩ በዝርዝር ማስረዳት ባይቻልም ዋናው ምክንያት የወያኔን ግፈኛ አገዛዝ እድሜ እያራዘመው ያለው መተባበር አለመቻላቸው እንደሆነ በመረዳታቸው ነበር:: ይህ የመተባበር ፍላጎት ግቡን ሳይመታ ግን ብዙ ዘመን አልፏል::

ፍላጎቱ እና ሙከራው ካልተሳካባቸው ምክንያቶች መሃል አንደኛው በየድርጅቶቹ አማካይነት ይቀርቡ የነበሩ የማይጣጣሙ የትብብር ቅድመ-ሁኔታዎች ሲሆኑ፣ ሌላው የፖለቲካ ድርጅቶቹ የማይታረቁ የፖለቲካ ግቦች ነበሩ:: በአንድነት እና በመለየት እንዲሁም በፖለቲካና ዴሞክራሲ ጥያቄ ዙሪያ የነበሩት ልዩነቶች በጋራ ተባብሮ ለመስራት የነበረውን ፍላጎት ሲያደናቅፉት ኖረዋል:: ይህ ሲጀመርና ሲቆም የነበረ የትብብር ፍላጎት እስከ ግንቦቱ ምርጫ ደረሰ:: ወያኔን ዲቃወሙ የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ቅንጅትን ጨምሮ ከወያኔ ጋር ባደረጉት ክርክር ከኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደት እንዳይሳተፉ በወያኔ የተከለከሉ ድርጅቶች ለሀገር ሰላም፣ አንድነት እና ለዴሞክራሲ ሲባል ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የሚሳተፉበት ውይይት እንዲጀመር ሲወተውቱ ነበር::

የግንቦቱ ምርጫ በወያኔ ከተጭበረበረ በኋላ በተፈጠረው ቀውስ የተነሳ፣ በቅንጅት እና በህብረቱ የቀረበው የብሄራዊ አንድነት መንግስት ሃሳብ ህጋዊ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ብቻ ሳይሆን ኦነግን የመሳሰሉ የነጻነት ግንባሮችን ያካተተ እንዲሆን ጠይቆ ነበር:: ይህም መንግስት በአስቸኳይ ለዴሞክረሲያዊ ምርጫ እና ስርአት የሚያስፈልጉትን ተቋሞች በማቋቋም አዲስ ምርጫ የሚደረግበትን ሁኔታ ያመቻቻል ተብሎ ታስቦ ነበር::

በኦነግም በኩል ከምርጫው በፊት እና በኋላም በወያኔ በኩል የቀረበውን «ያለምንም ቅድመ- ሁኔታ በአንድነት እንስራ» የሚል ጥሪ አልቀበልም በማለት፣ ጥሪው ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶች ያካተተ መሆን እንዳለበት በመግለጽ ቅንጅትን እና ህብረትን ከመሳሰሉ ድርጅቶች ጋር ለመስራት ያለውን ፈቃደኛነት ያረጋገጠበት ምላሽ ሰጥቷል::

ዩትሬክት ላይ የተፈጠረው ትብብር የሃገራችንን ፖለቲካ በሚመለከት ኦነግና ቅንጅት የደረሱበትን የፖለቲካ ግንዛቤ እና ብስለት የሚጠቁም ነው:: ይህ ትብብር ወያኔ ከግንቦቱ ምርጫ በኋላ በቅንጅት ድርጅት አባላትና ደጋፊዎች ላይ በወሰደው እመቃ የተነሳ «የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው» ከሚል ጊዚያዊ ስልት ጋር የተያያዘ አለመሆኑን ትብብሩን ለመፍጠር ከቅንጅት መፈጠር በፊት እና ከተፈጠረም በኋላ በእዚህ ጥያቄ ላይ ስለነበረው አመለካከት ከላይ የተሰጠው ገለጻ የሚያስረዳ ይመስለናል:: የትብብሩ መሳካት የረጅም ጊዜ እድሜ ያለው የተለያዩ አካለት የተናጠል እና የጋራ ፍላጎትና የስራ ውጤት ነው::

## ለ- ከትብብሩ መመስረት በፊት የተደረጉ ውይይቶች እና የውክልና ጥያቄ

የትብብሩ ስምምነት በዩትሬክት ከመፈረሙ በፊት ተከታታይ ውይይቶች፣ ዱባይ ከ 10-11/03/2006 እና ፍራንክፈርት ከ17-18/ 04/2006 ላይ ተደርገዋል:: እነዚህ ውይይቶች ቀደም ባሉ ግዜያት በሚስጥር እና በጥንቃቄ ሲደረጉ የነበሩት ጥረቶች ውጤቶች ናቸው:: የቅንጅት ከፍተኛ አመራር በወያኔ እስር ቤት ውስጥ ታፍኖ በተያዘበት ሁኔታ እንዲህ አይነቱ መሰረታዊ ሰነድ በሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅት ስም መፈረሙን በሚመለከት የሚቀርቡ ጥያቄዎች እንዳሉ ይታወቃል:: የቅንጅት አለምአቀፍ የፖለቲካ አመራር ኮሚቴ ለቅንጅት አባላት፣ ደጋፊዎች እና ለአጠቃላይ ህብረተሰቡ መግለጽ የሚፈልገው የሚቀጥለውን ሃቅ ነው:: የውክልና ጥያቄ የሚያነሱትን ወገኖች በዚህ ረገድ ያላቸውን ስጋት ለመቀነስ ስንል በተለይ በአሁኑ ወቅት ሁሉን ዘርዝረን መናገር የማንችል መሆኑን ነው:: መታወቅ የአለበት አንድ ቁም ነገር ግን፣ የትብብሩ ጉዳይ የተፈጸመው በጥቂት ግለሰቦች የግል ውሳኔ እንዳልሆነ ነው::

በሁኔታዎች አስገዳጅነት የአለም አቀፍ የፖለቲካ አመራር ኮሚቴው በሚገባ ባልተዋቀረበት የተከናወነ ቢሆንም አብዘኛዎቹ የአመራሩ አባላት የድርድሩን ሂደት እና ውሳኔ የሚያውቁት መሆኑን እንገልጻለን:: የአለም አቀፍ ኮሚቴው በቅርቡ ባደረገውና ሁሉም አባላቱ በአካል በተገኙበት የመጀመሪያ መደበኛ ስብሰባ በትብብሩ ላይ የቀረበለትን ሪፖርት በማጽደቅና የትብብሩን ሃላፊነት በመረከብ ለትብብሩ ትልቅ ትርጉም በመስጠት እንደሚነቃነቅ ስምምነት ላይ ደርሷል:: በትብብሩ ስምምነት ሰነድ ላይ የተጠቀሰውን የማሻሻያ መብት በመጠቀም ከአባላትና ከህዝብ ባገኘው ጥቆማ ያሰባሰባቸውን ማስተካከያ ሃሳቦች በትብብሩ ሰነድ እንዲካተቱ ለማድረግ ጥረት የሚያርግ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ እንገልጻለን::

*ሐ-- የስምምነቱ አላማ*

የስምምነቱ አላማ  አንድ ብቻ ነው:: ስምምነቱ ሃገራችን በአሁኑ ወቅት ከገባችበት የፖለቲካ ቀውስ የምትወጣበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው:: የዚህ ቀውስ መፍትሄ በአስቸኳይ በግንቦት ተጀምሮ ታላቅ ተስፋ ፈንጥቆ የነበረውን የዴሞክራሲ ሂደት ኢህአዴግ ገፍቶ ካስወጣበት ሃዲድ ላይ መልሶ ማስገባት ይሆናል:: ትብብሩ ይህንን ለማድረግ በሃገራችን የፖለቲካ ጉዳይ ያገባኛል የሚሉ የፖለቲካ እና ፖለቲካዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሙሉ በአንድ ላይ ተቀምጠው በጋራ የሚመክሩበት ጉባኤ እንዲዘጋጅ ማድረግ አስፈላጊ ነው ብሎ ያምናል:: በዚህ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ ወያኔ እራሱም ቢሆን እንደ አንድ የፖለቲካ ድርጅት መሳተፍ እንደሚችል ተገልጧል:: ጉባኤው ሰላማዊ እና ፍትሃዊ የሆነ የስልጣን ሽግግር መደረግ የሚችልበትን የዴሞክራሲ አግባብ ለመንደፍ የሚችል ይሆናል:: ይህ አግባብ ምን ይመስላል የሚለው ጥያቄ በጉባኤው ላይ የሚነሳና የሚወሰን ይሆናል:: ከጉባኤው በፊት ግን ፖለቲካ ድርጅቶች የየራሳቸውን ዝግጅቶች በማድረግ በተናጠል ይሁን በጋራ የመፍትሄ ሃሳቦች ይዘው እንዲመጡ ይጠበቅባቸዋል:: ትብብሩ በእዚህ ጉዳይ ላይ የደረሰበት ስምምነት የለም:: የተፈጠረው መቀራረብ ከተጠናከረ ቅንጅት እና በትብብሩ የገቡት ድርጅቶች የጋራ ስምምነት ለመድረስ የሚችሉበት ሁኔታ ይፈጠራል የሚል እምነት የቅንጅት አለም አቀፍ አመራር አለው::

የትብብሩ ፍላጎት የወያኔ መንግስት በመላው ኢትዮጵያ የሚያኪያሂደውን እመቃ በአስቸኳይ እንዲያቆም ነው:: በየእስር ቤቱ ያጎራቸውን መሪዎችና ንጹህ የሃገሪቱን ዜጎች በአስቸኳይ እንዲፈታ ነው:: በየቦታው በወያኔ እመቃ የተነሳ እየተቀሰቀሰ ያለው የአመጽ ትግል ሃገሪቱን እና አካባቢውን ለከፍተኛ አደጋ ሳያጋልጥ ከፖለቲካ ህይወታቸን ጠመንጃ የምናስወግድበትን ሰላማዊ የእርቅ እና የዴሞክራሲ መንገድ መተለም ነው:: ይህ አላማ ከቅንጅት መሰረታዊ እምነቶች ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው::

ከዚህ በላይ ከተባለው በተጨማሪ በቅንጅት በኩል ትብብሩ ከፍተኛ ሃገራዊ ትርጉም አለው:: *ኢህአዴግ ከስልጣን ላለመውረድ ሊጠቀምባቸው ካስቀመጣቸው የመጨረሻ ፈንጅዎች መሃከል ዋነኛው የኢትዮጵያን ህዝብ እርስ በእርሱ ማጫረስ ነው:: የእዚህን እኩይ ሴራ ፍንጩን በተደጋጋሚ አይተነዋል:: ይህ ትብብር በአሁኑ ጊዜ መፈጠሩ እንዲህ አይነቱ የኢህአዴግ እኩይ ሴራ በስራ መተርጎም እንዳይችል ለማድረግ ዋናው መከለከያ ነው::*

### መ- የቅንጅት መሰረታዊ የፖለቲካ እምነቶች እና ትብብሩ ያስነሳቸው ጥያቄዎች::

በዚህ ጉዳይ ላይ የምናተኩረው በመሰረታዊ ነጥቦች ላይ ይሆናል::

#### መ-1 የኢትዮጵያን ልእዋላዊ አንድነት አስመልክቶ፣

ቅንጅት በዚህ ትብብር ውስጥ ሲገባ የማናቸውንም ድርጅቶች የፖለቲካ ግብ ተቀብሎ አይደለም:: ሌሎችም ድርጅቶች በተመሳሳይ የቅንጅትን የፖለቲካ ግብ ተቀብለው አይደለም:: ዋናው መሰረታዊ እምነት እና ስምምነት ሁሉም ድርጅቶች የፖለቲካ ፕሮግራማቸውን ለህዝብ አቅርበው በህዝብ ለመዳኘት ፈቃደኛነታቸውን ማረጋገጣቸው ነው:: «አስቀድሞ የዚህ ወይም የዚያ ህዝብን ፍላጎት የማውቀው እኔ ነኝ:: እኔ በህዝብ ስም ውሳኔ እወስናለሁ:: ሌላ ፍጥረት በእዚህ ጉዳይ አያገባውም» የሚሉ አመለካከቶች በማይኖሩበት ሃገራዊ፣ ነጻና ዴሞክራሲያዊ የምርጫ ሂደት በህዝብ ድምጽ ለመገዛት በመተማመን የተደረሰ ስምምነት ነው:: የትብብሩ አላማ፣ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ ተሳክቶ፣ ለዴሞክራሲያዊ ሽግግር የሚደረገው ዝግጅት ከተጠናቀቀ በኋላ በፖለቲካ ድርጅቶች ፖሊሲዎች ላይ ህዝብ ፍርድ ሰጪ ይሆናል የሚል ነው::

ቅንጅት በእንዲህ አይነቱ መንገድ በሚፈጠር ዴሞክራሲያዊ መድረክ በፕሮግራሙ ውስጥ ያሰቀመጠውንና ባለፈውም ምርጫ አብላጫው መራጭ የደገፈውን የኢትዮጵያን ሉአላዊ አንድነት የሚያስጠብቅ የፖለቲካ ድል መልሶ እንደሚቀዳጅ እምነት አለው:: ይህ ብቻ ሳይሆን በትብብሩ ውስጥም የገቡት ድርጅቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ሰላማዊ ህጋዊና ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ከተመቻቻ ከዚህ ቀደም የነበራቸውን የመገንጠል ጥያቄ ትተው ለሀገሪቱ ህዝብ በሙሉ በሚጠቅም የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ የራሳቸውን አስተዋጽኦ ያበረክታሉ የሚል እምነት አለን:: በኦነግ በኩል ከወዲሁ በኢትዮጵያ ፖለቲካ አያገባኝም ከሚል አመለካከት ወጥቶ የሀገሪቱ ህዝቦች ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ለሚያደርጉት ትግል ወሳኝ ሚና መጫወት እችላለሁ የሚል የአመለካከት ሽግሽግ ማድረጉ የቅንጅት ተስፋ ባዶ ሜዳ ላይ የተመሰረተ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው:: ትብበሩ በተደረገበት ወቅት ሆነ በኋላ በኦነግ፣ በኦብነግ፣ በኢህአግ እና በሲአግ በኩል የሚታየውን ቀናና በጎ ፍላጎት፤ ቅንጅት የሚተረጉመው እንደ እውነተኛ የእምነት ጽናት እንጂ ከስልታዊ ብልጣብልጥነት አንደመነጨ አይደለም::

ቅንጅት የአንድነት ጥያቄ ለድርድር አይቀርብም ሲል የራሱን ድርጅታዊ እምነት ማስቀመጡ ነው:: ይህ እምነት ጭፍን እምነት አይደለም:: በምክንያት ላይ የተመሰረተ ነው:: የሃገራችንን እና የህዝቧን የረጅም ዘመን ታሪክ በሚገባ ከማጤን የመጣ ነው:: በኢትዮጵያ አንድነት አማራጭ የሌለው ጉዳይ መሆኑን በመረዳት ነው:: የሃገራችን ለዘመናት የቆየ እና አሁንም ያለው እውነታ የሚያሳየው ከአንድነት ውጭ ያለውን እውነታ የጋራ ውድመት ብቻ እንደሆነ ቅንጅት ስለሚያምን ነው:: ቅንጅት አብላጫውን ድምጽ ህዝብ ከሰጠኝ አንቀጽ 39 ከህገመንግስቱ በህዝብ ፈቃድ እሰርዛለሁ ብሎ በማኒፌስቶው ሲያስቀምጥ፣ ይህን የመገንጠል መበት የሚፈቅድ አንቀጽ በህገ-መንግስቱ ስለተገኘ ብቻ ሃገር ይፈራርሳል የሚል ስጋት ስላለው አይደለም::

አንቀጹ በኢትዮጵያ ሁኔታ በተግባር መተርጎም የማይችል፣ በሚሰጠው የማይጨበጥ ተስፋ ህዝብ በአንድ ሃገር ውስጥ በጋራ ጥረት የጋራ ችግሮቹን እንዳይፈታ፣ ተከፋፍሎ ወደ ውስጥ ሳይሆን ወደ ውጭ እንዲያይ የሚያደርግ አላማው በከፋፍለህ ግዛ መርህ ላይ የቆመ እኩይ አንቀጽ ነው ብሎ ስለሚያምን ነው:: በኢትዮጵያ የግለሰቦች መብት ሆነ የብሄር ብሄረሰብ መብቶች መከበር የሚችለው፣ ለሰለም እጦት እና ለድህነት መፍትሄ ማግኘት የሚቻለው ኢትዮጵያ በምትባል ሉአላዊ የሆነች ሃገር ውስጥ በሚደረግ ትግል ብቻ ነው ብሎ ያምናል:: ከሰላም፣ ከእኩልነት፣ ከዴሞክራሲ እና ከብልጽግና ጥያቄ ጋር ቅንጅት የአንድነትን ጥያቄ አብሮ የሚያነሳው በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንደኛውን ከሌላው ለይቶ እውን ለማድረግ ስለማይቻል ብቻ ነው::

በበኩላችን ኦነግን ጨምሮ ይህንን እየተገነዘቡ የመጡ ድርጅቶች በርካታ ናቸው ብለን እናምናለን:: ትብብሩ ከመቼውም በላይ የመለያየት ወይም የመገንጠል አደጋ የሚያስቀር እንጂ አንድነትን ጉዳት ላይ የሚጥል ነው የሚል እምነት የለንም:: ቅንጅት በተጀመረው ትብብር ውስጥ በሚደረግ በጋራ የመስራት ሂደት የሃገራችን አንድነት የበለጠ አስተማማኝ የሆነ መሰረት ላይ ማስቀመጥ ይቻላል ብሎ ያምናል:: ቅንጅት የመገንጠል አላማ ካላቸው ድርጅቶች ጋር አልሰራም ስላለ ብቻ የመገንጠል አለማ ያላቸውን ድርጅቶች ህልውና ማጥፈት ጥያቄውንም እንዳያነሱ ማሰቆም ይቻላል የሚል እምነት የለውም::

«ቅንጅት ትልቅ ድርጅት ነው:: እየተዳከሙ ካሉ ድርጅቶች ጋር በሚያደርገው ግኙኝነት ነፍስ እየዘራባቸው ነው» ለሚለው አባባል ማስረጃው ምን እንደሆነ ባይታወቅም፣ ቅንጅት ታላቅነቱን በአንድ ሃገር ውስጥ ፍጹም የሆነ የፖለቲካ ሞኖፖሊ እንዲኖረው ለማድረግ የሚሰራ ድርጅት አይደለም:: ህዝባዊና ሃገራዊ እርባና ያላቸው እስከሆኑ ድረስ ድርጅቶች ከቅንጅት ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት ትልቅና ጠንካራ ሆነው ቢወጡ ችግር ነው ብሎ አያምንም:: የተባለው ርባና ከሌላቸውም ምንነታቸው የሚረጋገጠውና የሚከስሙበትም መንገድ ይህ ይሆናል::

ቅንጅት፣ የፖለቲካ አመለካከት ልዩነቶች በሙሉ ዴሞክራሲያዊ እና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ መፍትሄ አግኝተው መቃለል አለባቸው ብሎ ያምናል:: ከፖለቲካ ደጋፊዎች ብዛት የሚነሳ ድርጅታዊ ትምክህት በሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ላይ የሚኖር ንቀትና ማግለልን የሚያስከትል፣ በአንድ ሃገር ወስጥ ለሰላም እና ለዴሞክራሲ ለሚደረገው ጥረት እንቅፋት ነው:: የተወሳሰቡ ችግሮች ባሉበት ሃገር፣ ዴሞክራሲ የወሳኙን አብላጫ ቁጥር ለማግኘት የሚደረግ እሽቅድምድም መሆን አይችልም:: አነስተኛ ቁጥር ያለቸውን የህብረተሰብ ፍላጎቶች ለማስተናገድ በሩን መክፈት የማይችል ዴሞክራሲ በሃገራችን ስር መስደድ አይቻልም::

በሃገራችን የተጀመረው የፖለቲካ ትግል አንድን ድርጅት በዴሞክራሲ ስም ወደ ስልጣን ከማውጣት በስተቀር ሌላ ትርጉም እንደሌለው አድርጎ ማየት ታላቅ ስህተት መሆኑን ቅንጅት የሚወተውተውም ለዚህ ነው:: ቅንጅት በዋነኛነት ዴሞክራሲን የሁሉም ህዝብ የሰላም፣ የብልጽግና፣ የሰብአዊና የነጻነት መብቶች ማስከበሪያ መሳሪያ አድርጎ ያየዋል:: ለዚህ ነው ቅንጀት በግንቦቱ ምርጫ ህዝብ ለድርጅቴ የሰጠው ድምጽ ይከበርና ወደ ስልጣን

ልውጣ ከሚለው ጥያቄ ይልቅ ለሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች እና የሀገሪቱ ህዝብ የሚጠቅም የደሞክራሲያዊ ተቋማት ምስረታ ይቅደም የሚል አቋም የወሰደው:: ቅንጅት ወደ ትብብሩ የገባበትም መርህ ከጠባብ የድርጅቱ ጥቅም ጋራ የተቆራኘ ሳይሆን ከአጠቃላዩ የሀገሪቱ ህዝብ ጥቅም አንጻር እርባና ያለው ውጤት ያመጣል ብሎ በማመኑ ነው::

*መ-2 የወቅቱን ህገ-መንግስት ተቀብሎ ስለመስራት፣*

በአንድ በኩል ኢህአዴግ የሰለማዊ ዴሞክራሲያዊ ሽግግር አካል እንዲሆን የሚደረግ ጥሪ፣ በሌላ በኩል የወቅቱን ህገ መንግስት አልቀበልም በማለት መጀመር አይችልም:: በአንድ በኩል አለም አቀፍ ህብረተሰቡ «ኢህአዴግ ከስልጣን ከተወገደ በኢትዮጵያ እና በአካባቢው ሰላምና መረጋጋት ሊጠፋ ይችላል» በማለት ኢህአዴግን ከነወንጀሉ አቅፎ በተቀመጠበት ሁኔታ፣ በሌላ በኩል ህገ-መንግስቱን አንቀበልም በማለት ለሚጀመር የፖለቲካ እንቅስቃሴ ድጋፍ ይሰጣል ብሎ መጠበቅ የዋህነት ይሆናል:: የአለም አቀፍ ህብረተሰቡ በኢትዮጵያ የሚደረግ የፖለቲካ ለውጥ ህጋዊነትና ሰላምን የተከተለ እንዲሆን ይሻል:: አለም አቀፍ ህብረተሰቡ ህጋዊነትን በህገ መንግስቱ ስር ለመኖር በሚደረግ ስምምነት ብቻ የሚገለጽ ተግባር አድርጎ ነው የሚያየው::

ለኢህአዴግም ቢሆን የሚቀርብለትን የሰላም እና የእርቅ አጀንዳ ላለመቀበል የሚያቀርበው ክርክር ተቃዋሚዎቼ ህጋዊነትን ላለመከተል አውጀው የተነሱ ናቸው በማለት ነው:: ዛሬም በቅንጅት መሪዎች ላይ ያቀረበው የሃሰት ክስ የሚያጠነጥነው ህገ-መንግስቱን በመናድ ዙሪያ ነው:: የትብብሩ አላማ ኢህአዴግን ያካተተ ሀገራዊ ጉባኤ እንዲደረግ ለማድረግ እስከሆነና አለምአቀፍ ህብረተሰቡም ለዚህ የሚረዳ ዲፕሎማሲያዊ ጫና በኢህአዴግ ላይ እንዲያደርግ ከተፈለገ ጉባኤው የወቅቱ የሃገሪቱ ህገ መንግስት ተጠብቆ የሚደረግ መሆኑን በግልጽ ማሰቀመጥ ያስፈልጋል::

በሌላ በኩልም በትብብሩ የገቡ ድርጅቶች በህገ መንግስቱ የተደነገገውን ከመገንጠል ፍላጎታቸው ጋር የተሳሰረውን አንቀጽ 39ና የብሄረሰብ ፌደራሊዝም ለማስጠበቅ በማሰብ ትብብሩ በወቅቱ ህገ መንግስት ስር እንዲደረግ የሚያደርጉት ግፊት እንዳለ ቅንጀት ያውቃል:: በቅንጅት በኩል ይህ አንቀጽ እንደተጠበቀ፣ ነገር ግን ይህንን አንቀጽ ለማስወገድ እንደሚሻ በመግለጽ በህገ-መንግስቱ ስር በግንቦት 1997 ምርጫ መግባቱን እናስታውሳለን:: ያስመዘገበውንም ግዙፍ ድል ሁላችንም እናውቃለን:: ዛሬም ይህንን አንቀጽ እና ሌሎችንም ከህገ-መንግስቱ ለማስወገድ የሚፈልጋቸውን አንቀጾች ለማስፈጸም የህዝብ ይሁንታ እንደሚያገኝ ቅንጅት እርግጠኛ ነው:: ህዝብ የተቀማውን የመወሰን ስልጣን እንደገና የሚያገኝበትን ሁኔታ ለመፍጠር በዚሁ ህገ-መንግስት ስር ከመለየት ወደ አንድነት የሚወስደንን ትብብር በጋራ እንጀምር ከሚሉ ሃይሎች ጋር ለማድረግ የሚፈራበት ምክንያት የለም::

በኢትዮጵያ ዛሬ ያለው መሰረታዊ ችግር አንቀጽ 39 ሳይሆን ይህንን አንቀጽ እና ሌሎቸንም የፖለቲካ ጉዳዮች ለህዝብ ለማቅረብ የሚያስችል እና ከህዝብ በሚሰጥ ዳኝነት ለማደር የሚቻልበት ሁኔታ አለመኖር ነው:: የህዝብ ዳኝነት የሚሰማበት ሁኔታ መፍጠር በህገመንግስቱ ውስጥ ለተካተቱት ጻረ

ዴሞክራሲያዊ እና ጸረ አንድነት አንቀጾች ምላሽ መስጠት የሚቻልበትን ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ ማመቻቸት ይሆናል፡፡

ቅንጅት በሃገራችን ህገ-መንግስት ውስጥ የተካተተው አንቀጽ 39 በሌለበት ሁኔታም የፖለቲካ ድርጅቶች እና ደጋፊዎቻቸው የመገንጠል ጥያቄ ማንሳት እንደሚችሉ ያውቃል፡፡ በእንግሊዝ እና በካናዳ ውስጥ በስኮትላንድ እና በኩቤክ የፖለቲካ ድርጅቶች ትግል የተደረጉት የመገንጠል ጥያቄዎች ለሬፈረንደም አስከመቅረብ የደረሱበት ምክንያት በእነዚህ ሃሮች የመገንጠልን ጥያቄ የሚያበረታታ አንቀጽ በህገ-መንግስታቸው ስለተካተተ አይደለም፡፡ በዴሞክራሲ ስርአት ውስጥ ሰዎች ተሰባስበው ሰላማዊ እና ህጋዊ በሆነ መንገድ የሚያደርጉትን የፖለቲካ ትግል አንድ ቡድን ስላልወደደው ማስቆም አይቻልም፡፡ የኢትዮጵያን ሁኔታ ለየት የሚያደርገው በኩቤክ እና በስኮትላነድ ጉዳይ ላይ ለመፍትሄነት የቀረበውን ሃሳብ ተግባራዊ ለማድርግ ቀርቶ ለማሰብ የሚያስችል ምንም አይነት ሀገራዊ እውነታ አለመኖሩ ብቻ ነው፡፡ ይህ እየታወቀ የፖለቲካ ድርጅቶች የመገንጠል ጥያቄቸውን ካልተው፣ ወይም አንቀጽ 39ን ካልተቃወሙ፣ በአንድነት ለደሞክራሲ የሽግግር ስርአት በጋራ ለመስራት እና ሂደቱም በሚፈጥረው መቀራረብ ለሚፈጠረው በጎ ፈቃድ እድል እንስጥ ለሚለው ጥሪያቸው አሉታዊ ምላሽ ቅንጅት ቢሰጥ ታሪካዊ ሃላፊነትን አለመወጣት ይሆን ነበር፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ ኦነግ የአንድነትንም ጥያቄ እንደ አጀንዳ ማንሳትና መነጋገር የሚቻልበትን የትብብር ሂደት እንጀምር ባለበት ወቅት ለጥሪው ምላሽ ቅንጅት ሰጥቷል፡፡ ቅንጅት እስከዛሬ ከተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር እንዳደረገው ሁሉ በእዚህ ትብብር ውስጥ የገባው በቅን ፍላጎት ነው፡፡ ይህ ቅን ፍላጎት በኦነግም በኩል እየተገለጸ ነው የሚል እምነት አለው፡፡ የዚህ ትብብር ስምምነት ቅንጅት በማኒፌስቶ ያስቀመጠውን እምነቱን ለማሰራጨት የሚከለክለው አይደለም፡፡ የአንቀጽ 39ንም ሆነ የመገንጠል የፖለቲካ አጀንዳ ለጥቂት የሃገሪቱ ህዝቦች ብቻ ሳይሆን ለሁሉም የሃገሪቱ ህዝቦች የማይጠቅም፣ እውቀትን፣ ጉልበትን እና ሃብትን በተግባር ሊተረጎም በማይችል ጉዳይ ላይ ማጥፋት ነው ብሎ ያምናል፡፡

ግለሰብ መብትን ያከበረ የብሄር-ብሄረሰቦች የእኩልነት ጥያቄ መልስ ማግኘት ያለበት ፍትሃዊ ጥያቄ መሆኑን ቅንጅት በማኒፌስቶው ግልጽ አድርጓል፡፡ ይሁንና የዚህ ጥያቄ ምላሽ የኢትየጵያን ህዘብ አንድነት ከማስጠበቅ ውጭ ይገኛል የሚል እምነት የለውም፡፡ በቅንጅት እና በትብብሩ አባል ድርጅቶች አማካይነት በሚደረገው መቀራረብ ይህንን እውነታ ሁሉም እንዲገነዘቡት ለማድርግ አስቸጋሪ አይሆንም የሚል ጽኑ እምነት ቅንጅት አለው፡፡

**ሠ--ጠመንጃ ካነሱ ድርጅቶች ጋር የቅንጀትን የሰላማዊ እምቢተኛነት ትግል ስልት በማነጻጸር፣**

ቅንጅት ትብብሩ ውስጥ የገባው ጠመንጃ ከሃገራችን የፖለቲካ ህይወት እንዲወጣ ለማድረግ ነው፡፡ ፖለቲካ ስልጡን እና ሰላማዊ ማህበራዊ እንቅስቃሴ እንዲሆን ለማድርግ ነው፡፡ ቅንጀት ጠመንጃ ከሃገራችን ፖለቲካ ይውጣ ሲል የነጻ አውጪዎቹ ጠመንጃ ብቻ ማለቱ አይደለም፡፡ የኢህአዴግ ፓርቲንም ጠመንጃ ጭምር ማለቱ ነው፡፡ ዛሬ በሃገራችን የሁሉንም ህዝብ ህገ -መንግስታዊ፣ የመናገር፣ የመሰብሰብ፣ የመጻፍና አልፎ ተርፎ የማሰብ ነጻነት በጠመንጃ ሃይል የገፈፈው በስልጣን ላይ

ያለው የኢህአዴግ መንግስት ነው፡፡ ትናንትናም ኦነግን ከነመሳሪያው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለድርድር የጠራው ከህግ ውጭ የቆመው የኢህአዴግ መንግስት ነው፡፡

በግንቦት 1997 ተጀምሮ የነበረውን ሰላማዊ እና ስልጡን የፖለቲካ እውነታ በአመጽ ያወደመው የኢህአዴግ ነው።

ቅንጅት፣ ይህ በነፍጥ የተደገፈ ፖለቲካ ለማንም አይበጅም በማለት ደጋግሞ ተናግሯል። በአስቸኳይ ሁሉንም ችግር መፍታት የሚቻልበት ሁሉን አቀፍ ጉባኤ ይጠራ በማለት ይህንን ጥሪ ለማሳካት ትብብሩን መስርቷል። የትብብሩ አላማ እንዲሳካ ቅንጅት አሁንም ቢሆን የሰላማዊ እምቢተኛነትን የትግል ስልት ይከተላል። የትብብሩ አባል ድርጅቶችም ቢሆኑ በነፍጥ የሚያደረጉትን ትግል ወደ ሰላማዊ እምቢተኛነት ትግል እንዲቀይሩ፣ አባላት እና ደጋፊዎቻችንን አስተባብረን በምንፈጥረው ሰላመዊ ግፊት፣ ወያኔም ነፍጠኛነቱን አውልቆ ወደጠራነው ጉባኤ እንዲመጣ ልናስገድደው እንችላለን።

ይህንን ለማድረግ የትብብሩ አባል ድርጅቶች በሚያደርጉት የተቀነባበረ የሰላማዊ እምቢተኛነት ትግል አስቸጋሪ አይሆንም። ከምስራቅ እስከ ምእራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ በሚቀጣጠል የህዝባዊ እና የሰላመዊ እምበተኛነት ትግል ኢህአዴግን ሆነ ያለ ኢህአዴግ ሌላ የሰላምና የመረጋጋት ዋስትና የማይታያቸውን አለም አቀፍ ህብረተሰብ ላቀረብነው የሁሉን አቀፍ ጉባኤ አወነታዊ ምላሽ እንዲሰጡ ማስገደድ ይቻላል። በቅንጅት እምነት ይህ የተሻለው የትግል ስልት አማራጭ ነው።

የነጻነት ግንባሮቹ መሳሪያቸውን አስቀምጠው በሰላማዊ መንገድ የፖለቲካ ትግል ለማድረግ እንደሚፈልጉ በትብብር ሰነዱ ላይ ፈርመዋል። «ሁላችንም መሳሪያችንን አስቀምጠን በሰላም የምንወያይበት ጉባኤ ይጠራ ብለዋል።» ከንግዲህ ለጥሪው ምላሽ መስጠት ያለበት ኢህአዴግ ነው። ባለንበት ሁኔታ አመጽን ከህገራችን የፖለቲካ ህይወት ነጻ ለማድረግ የሞራል የበላይነቱ ያለው፣ የራሱ ጠመንጃ ያዥ ቡድን የሌለው ቅንጅት ብቻ ነው። በአፋጣኝ ሰላማዊ የፖለቲካ ሂደት እንዳይጀመር ዋነኛው ችግር ፈጣሪ ኢህአዴግ ነው። እስከአሁን ድረስ የአመጽ ጥፋትን በማቀጣጠል ተጠያቂው የተነጠፈለትን የሰላም ዘንባባ የሚረግጠው የኢህአዴግ መንግስት እንጂ ቅንጅት አይደለም።

በሌላ በኩልም ከግንቦት 97 በኋላ በሃገራችን የተቀጣጠለው የነጻነት ፍላጎት በወያኔ ምትክ ሌላ ባለጠመንጃ አምባገነን ሃይል የሚተካበትን ሁኔታ የማይፈቅድ ነው የሚል እምነት ቅንጅት አለው። በትብብሩ ውስጥ ህብረትን እና ሌሎችንም የፖለቲካ እና የሲቪል የፖለቲካ ድርጅቶችን፣ እንዲሁም ጠመንጃቸውን አስቀምጠው በተጠራው ጉባኤ ውስጥ ለመሳተፍ ፈቃደኛ የሚሆኑትን ሌሎች ቡድኖች የትብብሩ አካል እንዲሆኑ በማድረግ፣ የትብብሩን መሰረት በማስፋት ትብብሩ ጠመንጃ በያዙ የፖለቲካ ድርጅቶች የበላይነት ስር እንዳይወድቅ ማድረግ ይቻላል የሚል እምነት ቅንጅት አለው። እንዲህ አይነቱን አደጋ መከላከል የሚችልባቸውን ስልቶች በማጥናት ተግባራዊ ማድረግ ከቅንጀት ሃላፊነቶች አንዱ እና ዋነኛው እንደሆነ እንገነዘባለን።

ረ- ትብብሩ እና የጎረቤት ሃገሮች ጉዳይ፣

የትብበሩ ሰነድ ደጋግሞ እንደሚያነሳው አላማው በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአካባቢው ሰላምና መረጋጋትን የሚያመጣ ቋሚ መፍትሄ መሻትም ጭምር እንደሆነ ገልጧል። በተለይ ከጎረቤት ሃገሮች ኤርትራን በስም በመጥቀስ በኢትየጵያ እና በኤርትራ መሃል

ያለውን ፍጥጫ ሰላማዊ በሆነ መንገድ በሁለቱም ሀገሮች እና ህዝቦች ስምምነት እልባት እንዲያገኝ ጥረት እንደሚያደርግ አትቷል። ይህ የጥረት ሃሳብ በሰነዱ የተካተተው «በአስመራው መንግስት እና በኦነግ መካከል» ባለው የጠበቀ ግኙኝነት የተነሳ እንደሆነና እንዲያውም ጠቅላላ የሰላም እና የእርቅ ጉባኤው ሃሰብ ሳይቀር

የሻብያ አጀንዳ ነው አስከማለት የደረሱም አሉ፡፡ በእኛ በኩልም ኦነግም ይሁን ሌሎቸም ድርጅቶች እንደወያኔ/ኢህአዴግ በኤርትራ ምድር ይንቀሳቀሱ እንደነበር እና አሁንም በአስመራ ውስጥ ጽህፈት ቤት እንዳላቸው እናውቃለን፡፡ ይሁንና ለትብብሩ በኦነግ በቀረበውና ሰምምነት በተደረሰበት ሰነድ ውስጥ የኤርትራን ብሄራዊ ጥቅም በኢትዮጵያ ብሄራዊ ኪሳረ የሚያጠናክር ነገር አይታይም፡፡ የሃገራችንን አንድነት የሚያናጋ እና ጥንካሬዋን የሚንድ አላማ ከሰነዱ ውስጥ ፈትሸን ማግኘት አንችልም፡፡ የመገንጠል ጥያቄያቸውን በመተው ወይም ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለህዝብ ለማቅረብ፣ ወያኔን ጭምር ያካተተ ጉባኤ እንዲጠራ የሚያደርግ ትብብር ኢትዮጵያን አዳክሞ የሚባለውን የሻብያ ህልም ሲያሳካ አይታየንም፡፡

በሁለቱም ወገን ከግማሽ ሚሊዮን የሚበልጡ ወታደሮች ተፋጠው ለሌላ ዙር እልቂት በተጠንቀቅ የቆሙበት እውነታ አይናችንን ብንጨፍንም አይጠፋም፡፡ መዘዙ፣ ቅንጅትን ሌት ተቀን የሚያሳሰበውን የሃገራችንን ሰላም ጭራሽኑ አጥፍቶ፣ ድህነትን አባብሶ፣ ጦርነት በራሱ በሚፈጥረው አፋኝ ሁኔታ ዴሞክራሲን ቀብሮና አንድነትን አናግቶ የሚጠቃለል ነው፡፡ በጦርነት መቀስቀስ ያሰፈሰፈን የውድመት መአበል ለማስቀረት በትብበሩ ሰነድ ላይ ችግሩ በሰላመዊ ሁኔታ እንዲፈታ ምኞትን እና ፈቃደኛነትን ማሳየት ተገቢ ነው፡፡ በሻብያ እና በኢህአዴግ መሃል የሚነሳው ግጭት የትብብሩን አላማ መና ሊያስቀረው የሚችልበት አደጋ ገሃድ ሆኖ እየታየ ሰበብ አስባብ እየፈጠሩ ችግሩን አለማንሳት ጭንቅላቷን ብቻ አሸዋ ወስጥ በመቅበር ተደብቄያለሁ እንዳለቸው ሰጎን መሆን ነው፡፡

ቅንጅት በማኒፌስቶውም እንዳስቀመጠው በኢትዮጵያ እና በኤርትራ መሃከል የሚኖረው ግኑኝነት የሁለቱንም ህዝቦች የዘለቄታ ጥቅም በማስጠበቅ ላይ የተመሰረተ ብቻ ነው መሆን የሚችለው፡፡ ቅንጅት ጽፈት ቤታቸው አስመራ ላይ ከሆኑ ድርጅቶች ጋር ትብብር ፈጠረ ማለት ቅንጅት የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም ለማስከበር ከኤርትራ ጋር መደረግ ያለበት አጠቃለይ ስምምነት በማለት በማኒፌስቶው ያስቀመጣቸው የፕሮግም ነጥቦች ተሰርዘዋል ማለት አይደለም፡፡ ትብብሩ ለሰው የማይታይ ስውር የሻብያ ጠቀሜታ አለው የሚሉ ወገኖቻችን ይህ ለሰው ያልታየ የሚሉትን ጉዳይ ገላልጠው ካላሳዩን ፍራቻቸው አንድም የአስመራውን መንግስት እና ባለስልጣናቱን ከኢትዮጵያዊያን የላቁ ጥበበኞች አድርገው የሚሸበሩ፣ አሊያም የሚናገሩትን የማየውቁ ናቸው የሚል እምነት አለን፡፡

ቅንጅት በራሱ እና ለሃገሩ ቀናኢ በሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ የሚተማመን ድርጅት ነው፡፡ በመሆኑም የሚቀርብለትን የፖለቲካ አማራጭ በሁሉ አቅጣጫ መርምሮ ለህዝብ ለሃገር ይበጃል የሚለውን ውሳኔ ይወስናል፡፡ ትብብር ለነጻነት እና ለዴሞክራሲ በቅርብ ጊዜ በሃገራችን ከተከሰቱት የሰላምና የአንድነት የነጻነትና የዴሞክራሲ ጠባብ ቀዳዳዎች አንዱ በመሆኑ በትብበሩ ውስጥ በሚገባ በመሳተፍ ለትብብሩ መሳካት አስፈላገውን ጥረት ያደርጋል፡፡ የትብብሩ ጥሪ በተደረገበት ወቅት በቅንጅት በኩል የነበረው የፖለቲካ አመራር ክፍተት ፈጥሮት የነበረውን የተሳታፊነት ድክመት ማስተካከል የሚአስችል ሁኔታ ፈጥረናል፡፡ ይህ ሁኔታ አስከሚስተካከል በኦነግና በትብብሩ አባል ድርጅቶች በኩል ስራዎችን በመስራትም ይሁን ሃለፊነትን በመሸከም የተደረገውን ጥረት የቅንጅት አለም አቀፍ አመራር በበጎ እና በቀና መንፍስ የሚያየው ነው፡፡

የቅንጅትን የስራ ሃላፊነት በሚገባ ለመሸከም የሚያስችል ዝግጅት በማድረጋችን በሙሉ አቅሙ የትብብሩን ስራ ለመስራት ተዘጋጅተናል፡፡ በእዚህ ጥረት አማካኝነት በሚደረገው ትግል ከአምባገነንነት ወደ ዴሞክራሲ መሸጋገር የሚቻልበት መንገድ እንጠርጋለን ብለን እናምናለን፡፡ ይህ ትብብር ገና ከጅምሩ በተለያዩ ማህበረሰብ አባለት መሃከል የቀረበ ግንኙነት እንዲፈጠር ማድረግ ችሏል፡፡ በግለሰቦች ይሁን በቡድኖች መሃከል የነበረ ጥርጣሬ ተፍቶ በመቀራረብ፣ በጋራ የመከራ ህይወታቸው ላይ

እንዲመክሩ በሩን ከፍቶላቸዋል። ከጥቂት ጊዜ በኋላም በሚሊዮኖች የሚቆጠሩት የጋራ መፍትሄ አንግበው በጋራ ይነሳሉ። በከፋፍለህ ግዛው ፖሊሲ ስልጣኑን ለዘላለም ተከላክሎ ማቆየት የሚቻል የመሰለው የመለስ ዜናዊ የጥቂት ዘረኞች ቡድን በትብብሩ መፈጠር ተሸብሯል። ያለው ምርጫ ይህ ትብብር የሰጠውን የሰላም እድል መጠቀም ብቻ ነው።

የዚህ ትግል የወዲያውኑ ግብ በግፍ የታሰሩ የቅንጅት መሪዎችን፣ ጋዜጠኞችን፣ የሲቪል ማህበራት መሪዎችን እና በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ኢሰብአዊ በሆነ ሁኔታ በየማጎሪያው ጣቢያ የተጠቀጠቁትን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ንጹህ የሃገሪቱን ዜጎች በማስፈታት የሚጀመር መሆን አለበት። ይህንን ለማሳካት በዲፕሎማቲክ መስኩ በተወሰደው እርምጃ ትብብሩ በአንድነት እንደሚቆም ለአለም አቀፉ ህብረተሰብ አረጋግጧል። ዘርና ሃይማኖት ሳንመርጥ የአንዱ ጥቃት የሁሉም ጥቃት እንደሆነ የሚያሳየውን የመጀመሪያውን ተጨባጭ እርምጃ ትብብሩ ወስዷል። ለእዚህ ትብብር አላማ መሳካት የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም ሁሉም ለሰላም ለአንድነት እና ለዴሞክራሲ የቆሙ የሃገሪቱ ዜጎች በሙሉ የሚቻለውን ጥረት እንዲያደርጉ የቅንጅት አለም አቀፍ የፖለቲካ አመራር ጥሪውን ያቀርባል።

***<u>ትብብሩ ያለመውን የነጻነት፣ የዴሞክራሲ የእኩልነት እና የአንድነት ህልም ለማሳካት እንነሳ!</u>***

***<u>የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት ብቸኛው የሰላም የእኩልነት የነጻነት እና የዴሞክራሲያዊ ዋስትና ነው!</u>***

***የቅንጀት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ***
***አለም አቀፍ የፖለቲካ አመራር ኮሚቴ***

***ሰኔ 23 1998***
***ዋሽንግተን ዲሲ***